የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 42
ADDIS ABABA, 10th July, 2024

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴/፳፻፲፮

ለፓወር ሴክተር ሪፎርም፣ ኢንቨስትመንትና ሞደርናይዜሽን ፕሮጀክት ምዕራፍ አንድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ……….…………………......ገጽ ፲፭ሺ፯፻፮

## Content

Proclamation No. 1330/2024

International Development Association Loan Agreement for financing Power Sector Reform, Investment and Modernization in Ethiopia Project as Phase 1 of a Multiphase Programmatic Approach (MPA)), Ratification Proclamation..........Page 15706

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴/፳፻፲፮

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለፓወር ሴክተር ሪፎርም፣ ኢንቨስትመንትና ሞደርናይዜሽን ፕሮጀክት ምዕራፍ አንድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ፫፻፺፫ ሚሊዮን (ሶስት መቶ ዘጠና ሶስት ሚሊዮን) ኤስ ዲ አር ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፳፱ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1330/2024

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELPOMNET ASSOCIATION

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association stipulating that International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to SDR 393,000,000 (Three Hundred and Ninety-Three Million SDR) Special Drawing Rights for Power Sector Reform, Investment and Modernization in Ethiopia Project as Phase 1 of a Multiphase Programmatic Approach (MPA)), was signed in Addis Ababa on 7th day of April, 2024;

ይህን ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሂደው ፳፱ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. ይጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለፓወር ሴክተር ሪፎርም፣ ኢንቨስትመንትና ሞደርናይዜሽን ፕሮጀክት ምዕራፍ አንድ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መጽደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7520-ET በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

**፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፫፻፺፫ ሚሊዮን (ሶስት መቶ ዘጠና ሶስት ሚሊዮን) ኤስ.ዲ.አር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS**, the House of peoples' Representatives of the Federal Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 30th day of May 2024;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing Power Sector Reform, Investment and Modernization in Ethiopia Project as Phase 1 of a Multiphase Programmatic Approach (MPA)), Ratification Proclamation No. 1330/2024".

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement Number 7520-ET signed in Addis Ababa on 7th day of April, 2024 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to SDR 393,000,000 (Three Hundred and Ninety-Three Million SDR) Special Drawing Rights in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 10th Day of July, 2024**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**